በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No 1.0/34/09
ቀን / Date 25 ነሐሴ 2009.

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ ፡- <u>የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፤</u>

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የታክስ ክሊራንስ እንዲሰጣቸው የአገልግሎት ጥያቄ የሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች በቅድሚያ ኦዲት መደረግ ያለባቸው እና የሌለባቸውን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 128/2009 ሥራ ላይ እንዲውል የተላከ መሆኑን እስታውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ገ/መድህን

<u>ግልባጭ</u>

ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት

ለአገር ውስጥ ታክስ ፕ/ልማትና ድጋፍ ሥ/ ዘርፍ

ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ

ለሕግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ

ለሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ሥራዎች ዘርፍ

ለአዲስ አበባ አገር ውስጥ ታክስ ፕ/ልማትና ድጋፍ ሥ/ ዘርፍ

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

ዳይሬክቶሬቶች፡-

- ለፌደራል አገር ውስጥ ታክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለፌደራል አገር ውስጥ ታክስ የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለፌደራል አገር ታክስ ኦዲት አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለፌደራል አገር ውስጥ ታክስ ደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ቅ/ጽቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ- ዕቃ አወጣጥ ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ሕግ ተገዥነትና ሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተሊጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለድንበር አስተዳደርና ኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትመንት ደጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለዕቅድና አፈፃፀም ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለተያዙና ለተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለጥናትና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ሥራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለለውጥ ትግበራ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት
- ለግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለክልሎች ድጋፍና ትብብር ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለትምህርትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
- ለሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለአገር ውስጥ ታክስ አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለኢንቨስትጌሽን ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለአዲስ አበባ አገር ውስጥ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለአዲስ አበባ አገር ውስጥ ታክስ የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል ፕ/ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለአዲስ አበባ አገር ታክስ ኦዲት አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለአዲስ አበባ አገር ውስጥ ታክስ ደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፡-

- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

  አዲስ አበባ

- ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  አዳማ

- ለሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ሞጆ

- ለባህርዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ባህርዳር

- ለመቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  መቀሌ

- ለሀዋሳ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ሀዋሳ

- ለድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ድሬደዋ

- ለኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ኮምቦልቻ

- ለሚሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ሚሌ

- ለጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ጅግጅጋ

- ለሞያሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ሞያሌ</u>

- ለጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ጅማ</u>

- ለጋላፊ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>ጋላፊ</u>

- ለአዲስ አበባ ቁጥር 1 መካ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቁጥር 2 መካ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመርካቶ ቁጥር 1 /ቅ/ጽ/ቤት
- ለመርካቶ ቁጥር 2 /ቅ/ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክ/ከ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለየካ ክ/ከ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክ/ከ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአራዳ ክ/ከ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ ከተማ ክ/ከ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክ ክ/ከ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለልደታ ክ/ከ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት

  <u>በያሉበት</u>

# በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

በታክስ ክሊራንስ ጥያቄ በቅድሚያ ኦዲት መደረግ

ያለባቸውና የሌለባቸው ግብር ከፋዮችን

ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 128/2009

ነሐሴ/2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የታክስ ኦዲት አሰራር የስጋት ሥራ አመራር ላይ የተመሰረተ ነው ቢባልም በተጨባጭ የታክስ ኦዲት አፈጻጸም በአመዛኙ በግብር ከፋዮች የአገልግሎት ጥያቄ ላይ የተመሰረተ መሆኑንና የኦዲት ሥራችን በስጋት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ፤

በግብር ከፋዮች ለቀረቡ የተለያዩ የአግልግሎት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የኦዲት ሥራ በቅድመ ሁኔታነት በመቀመጡ ምላሽ ሳያገኙ ዓመታትን ያስቆጠሩ የግብር ከፋዮች የአገልግሎት ጥያቄ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ስለሚገኝ በዚህም ምክንያት ግብር ከፋዮች ለምልልስና ለእንግልት እየተዳረጉ በመሆኑ እና ያለውን ውስን የሰው ሀብት ውጤት ሊያስገኙ በሚችሉ የኦዲት ሥራዎች ላይ ለማሰማራት፤

የአገልግሎት ጥያቄዎችን እንደ ስጋት ደረጃቸው በሌሎችም የሥራ ክፍሎች ማለትም የታክስ አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል እና የደንበኞች አገልግሎት በዚህ መመሪያ በተቀመጠው የአሰራር ሥርዓት መሰረት እንዲፈጸም እንዲሁም የታክስ ኦዲት አሰራር በታክስ ኦዲት ፖሊሲ መሰረት የስጋት ሥራ አመራር ላይ ተመስርቶና ትኩረት ሰጥቶ እንዲከናወን ለማስቻል፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "በታክስ ክሊራንስ ጥያቄ በቅድሚያ ኦዲት መደረግ ያለባቸውና የሌለባቸው ግብር ከፋዮችን ለመወሰን የወጣ መመሪያቁጥር 128/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፦

1) **"የአገልግሎት ጥያቄ"** ማለት በተለያዩ መነሻዎች የግብር ዕዳ የሌለበት ስለመሆኑ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ግብር ከፋዩ ለባለሥልጣኑ የሚያቀርበው ጥያቄ ነው፤

2) **"ስጋት"** ማለት የባለሥልጣኑ ዓላማ እንዳይሳካ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ክስተቶች ማለትም ግብር/ታክስ ማጭበርበር፣ ታማኝ ያለመሆን፣ ያልተገባ የግብር/ታክስ ተመላሽ መጠየቅ እና ኪሣራ ማስታወቅ ወዘተ በአጠቃላይ የታክስ ሕጉችን አክብሮ አለመስራት ነው፤

3) **"የስጋት ደረጃ"** ማለት የተጠኑ እና የተለዩ ስጋቶችን እንደሚያስከትሉት ኢኮኖሚያዊ ጉዳት መጠን በቅደም ተከተል በከፍተኛ፣ በመካከለኛ እና በዝቅተኛ ስጋት ደረጃ በመከፋፈል መመደብ ነው፤

4) **"ከፍተኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በስጋት መምረጫ መስፈርት መሰረት ተቋሙ ባስቀመጠው ከፍተኛ የስጋት ወሰን ክልል (Range) ውስጥ ያረፈ የግብር ከፋይ የስጋት ድምር ውጤት (Total risk score) ሆኖ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የመፍጠር አቅም ያለው ማለት ነው፤

5) **"መካከለኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በስጋት መምረጫ መስፈርት መሰረት ተቋሙ ባስቀመጠው መካከለኛ የስጋት ወሰን ክልል (Range) ውስጥ ያረፈ የግብር ከፋይ የስጋት ድምር ውጤት (Total risk score) ሆኖ መካከለኛ አሉታዊ ተጽዕኖና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የመፍጠር አቅም ያለው ማለት ነው፤

6) **"ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በስጋት መምረጫ መስፈርት መሰረት ተቋሙ ባስቀመጠው ዝቅተኛ የስጋት ወሰን ክልል (Range) ውስጥ ያረፈ የግብር ከፋይ የስጋት ድምር ውጤት (Total risk score) ሆኖ ዝቅተኛ አሉታዊ ተጽዕኖና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የመፍጠር አቅም ያለው ማለት ነው፤

7) **"የታክስ ኦዲት"** ማለት በኦዲት ዕቅድ ውስጥ የተካተቱ ግብር ከፋዮችን የሒሳብ መግለጫና ደጋፊ ሰነዶች እንዲያቀርቡ በማድረግ መከፈል የሚገባው ያልተከፈለ ግብር/ታክስ ስለመኖሩ ጥልቅና ዝርዝር የሒሳብ ምርመራ በመስራት ማረጋገጥ ነው፤

8) **"ዴስክ ኦዲት"** ማለት በዴስክ ኦዲት ዕቅድ ውስጥ የተካተቱ ግብር ከፋዮች ያሣወቁትን ግብር/ታክስ ትክክለኛና ተሟልቶ መቅረቡን በእጃችን ካሉ መረጃዎችና

እንደአስፈላጊነቱ ከሶስተኛ ወገን ከሚገኙ መረጃዎች ጋር በማመሳከር መከፈል የሚገባው ያልተከፈለ ግብር/ታክስ ስለመኖሩ የሚከናወን የሒሳብ ምርመራ ነው፤

9) **"የንግድ ሥራ ሀብት"** ማለት የንግድ ሥራ በማከናወን ሂደት በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ ሀብት ነው።

10) **"አዋጅ/ጆች"** ማለት የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና የፌዴራል የታክስ አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ናቸው፤

11) በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላትና ሀረጎች በታክስ ህግ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የታክስ ክሊራንስ እንዲሰጣቸው የአገልግሎት ጥያቄ በሚያቀርቡ ማናቸውም ግብር ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የታክስ ኦዲት ክዋኔን በቅድመ ሁኔታነት የሚጠይቅ የክሊራንስ አገልግሎት ጥያቄ</u>

4. <u>የታክስ ክሊራንስ</u>

ማንኛውም ታክስ ከፋይ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሰረት የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል።

5. **<u>የታክስ ኦዲት ክዋኔን በቅድመ ሁኔታነት የሚጠይቅ የክሊራንስ አገልግሎት ጥያቄ</u>**

1) ድርጅት ለመዝጋት የሚቀርብ የክሊራንስ ጥያቄ በስጋት መምረጫ መስፈርት መሠረት ድርጅቱ ከፍተኛ ስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ ከመዘጋቱ በፊት በኦዲት መረጋገጥ ይኖርበታል።

2) ከ50% (ሃምሳ በመቶ) በላይ የንግድ ስራ ሀብት ለማስተላለፍ የቀረበ የአገልግሎት ጥያቄ በሚሆንበት ጊዜ:-

(ሀ) ለከፍተኛ እና ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ድርጅቱ በስጋት መምረጫ መስፈርት መሠረት ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ እና

(ለ) ለአነስተኛ ግብር ከፋይ ቅ/ጽ/ቤቶች የስጋት ደረጃ ግምት ውስጥ ሳይገባ ሁሉም የንግድ ሥራ ሀብት የማስተላለፍ አገልግሎት ጥያቄ በኦዲት መረጋገጥ ይኖርበታል።

3) ህጋዊ ህልውና የነበራቸው ድርጅቶች በአንድ ላይ ለመደራጀት ወይም ለመዋሀድ ጥያቄ አቅርበው ዋናው ድርጅት የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳን ጨምሮ የሚዋሃዱ ስለመሆኑ በፀደቀ ሰነድ ከቀረበ፡-

(ሀ) ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በቀጥታ በደንበኞች አገልግሎት በኩል ይስተናገዳል፤

(ለ) ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ በስጋት መምረጫ መስፈርት መሠረት ድርጅቱ ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ አገልግሎቱ ከመሰጠቱ በፊት በኦዲት መረጋገጥ ይኖርበታል፤

(ሐ) ዋናው ድርጅት የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳን ጨምሮ የማይዋሃድ በሚሆንበት ጊዜ የቀረበው የአገልግሎት ጥያቄ ድርጅት እንደ መዝጋት ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል፤

(መ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም የቀረበው ሰነድ ከፍተኛ ስጋት በሚያመለክትበት ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፉ በቅድሚያ ኦዲት ሊያደርገው ይችላል።

4) የቅድመ ግብር/ታክስ ተመላሽን በተመለከተ ለሚቀርብ ጥያቄ ለየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተቀመጠው የተመላሽ ጣሪያ መሠረት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አገልግሎቱ ከመሰጠቱ በፊት በውጪ ኦዲተሮች የድርጅቱ የሒሳብ መግለጫን አስመልክቶ የተገለፀው

(ሀ) አስተያየት ለመስጠት የማያስችል ወይም ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት ከሆነ ወይም/እና

(ለ) በሁኔታዎች የተገደበ አስተያየት የተሰጠበት ሆኖ ከግብር ወይም ታክስ ተመላሹ ጋር በተገናኘ አጠራጣሪ ነጥቦች መኖራቸው ሲታመን እንደ አስፈላጊነቱ አገልግሎቱ ከመሰጠቱ በፊት በኦዲት መረጋገጥ ይኖርበታል።

## ክፍል ሦስት

## በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ እና በደንበኞች አገልግሎት የሚስተናገዱ የአገልግሎት ዓይነቶች

6. **የድርጅትን ሀብት ስለመሸጥ ወይም ስለማስተላለፍ**

ከ50% (ሃምሳ በመቶ) በላይ የድርጅት ሀብት ስመሸጥ/ስማስተላለፍ ለከፍተኛ እና ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የሚቀርብ የአገልግሎት ጥያቄ ግብር ከፋዩ በስጋት መምረጫ መስፈርት መሠረት ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ ካልተገኘ በግብረ አወሳሰን የሥራ ክፍል በኩል በዴስክ ኦዲት ተጣርቶ አገልግሎቱ እንዲሰጥ ለደንበኞች አገልግሎት የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

7. **ድርጅትን በከፊልም ሆነ በሙሉ ስለመዝጋት**

ድርጅትን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመዝጋት የቀረበ የአገልግሎት ጥያቄ ሆኖ ድርጅቱ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ አጠቃላይ ኦዲት ማድረግ ሳያስፈልግ በግብር አወሳሰን የሥራ ክፍል በኩል በዴስክ ኦዲት ተጣርቶ አገልግሎቱ እንዲሰጥ ለደንበኞች አገልግሎት የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

8. **የካፒታል ሀብትን ስለማስተላለፍ**

የካፒታል ሀብቶችን (አክስዮን ባለቤት መብት) /Share/ ለማስተላለፍ የሚቀርብ ማንኛውም ጥያቄ በግብር አወሳሰን የሥራ ክፍል በኩል በዴስክ ኦዲት ተጣርቶ አገልግሎቱ እንዲሰጥ ለደንበኞች አገልግሎት የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

9. **ድርጅቶች በአንድ ላይ ስለማደራጀት**

የተለያዩ ህጋዊ ህልውና የነበራቸውን ድርጅቶች በአንድ ላይ ለማደራጀት ወይም ለማዋሀድ የሚቀርብ ጥያቄ ዋናው ድርጅት የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳን ጨምሮ የሚዋሀድ ስለመሆኑ በፀደቀ ሰነድ ካቀረበ እና በበጀት ዓመቱ የስጋት መምረጫ መስፈርት መሠረት ድርጅቱ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ በቀጥታ በደንበኞች አገልግሎት በኩል የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

10. **የድርጅት ሥም ወይም አድራሻ ስለመለወጥ**

የድርጅት ስም ወይም አድራሻ ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ የአገልግሎት ጥያቄ በቀጥታ በደንበኞች አገልግሎት በኩል የሚስተናገድ ሆኖ ግብር ከፋዩ ከቀድሞው ሥም ጋር

የተገናኙ የግብር/ታክስ ግዴታዎችን እንደሚወጣ በማመልከቻ ጽሁፉ ላይ ማቅረብ አለበት።

11. <u>ስለ ንግድ ዘርፍ ቅነሳ</u>

የንግድ ዘርፍ ቅነሳ ጥያቄ ሲቀርብና ይህም የሀብት ቅነሳን የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ (7) መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል። ነገር ግን የዘርፍ ቅነሳው ከሀብት ቅነሳ ጋር የማይገናኝ በሚሆንበት ጊዜ አገልግሎቱ በቀጥታ በደንበኞች አገልግሎት በኩል የሚሰጥ ይሆናል።

12. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ጥያቄ</u>

የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ጥያቄዎች ሲቀርቡ በተመላሽ ክፍል በኩል አሠራሩን ተከትሎ በሚደረግ የማጣራት ሥራ አገልግሎቱ የሚሰጥ ይሆናል።

13. <u>የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ስህተት</u>

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ስህተትና ሌሎች የመሣሰሉ ጥያቄዎች ሲቀርቡ በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሥራ ክፍል በኩል አሠራሩን ተከትሎ በሚደረግ የማጣራት ሥራ አገልግሎቱ የሚሰጥ ይሆናል።

14. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ ቁጥር (2) እና አንቀጽ 6 ከተጠቀሰው ውጪ ማንኛውም 50% (ሃምሳ በመቶ) በታች የንግድ ሥራ ሀብት ለማስተላለፍ የሚቀርብ ጥያቄ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤት በግብር አወሳሰን የሥራ ሂደት በኩል በዴስክ ኦዲት ተጣርቶ አገልግሎቱ እንዲሰጥ ለደንበኞች አገልግሎት የሚተላለፍ ይሆናል።

15. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ</u>

ከተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ በፊት ላለፉት ስድስት ወራት በነበሩ ግብይቶች እና ባልተሸጡ ዕቃዎች ላይ የግብዓት ይያዝልኝና የምዝገባ አገልግሎት ጥያቄ ሲቀርብ ጥያቄው በግብር አወሳሰን የሥራ ሂደት ተጣርቶ የምዝገባ አገልግሎቱ እንዲሰጥ ለደንበኞች አገልግሎት ይተላለፋል።

16. <u>የንግድ ሥራ ያልሰሩ ግብር ከፋዮች</u>

ግብር የሚከፈልበት የንግድ ሥራ ያልሠሩ ግብር ከፋዮች የንግድ ሥራቸውን ለመዝጋት ጥያቄ ሲያቀርቡ ከኢንተለጀንስ፣ ከታክስ መረጃ አስተዳደር፤ እንደ አስፈላጊነቱ ከባለድርሻ አካላት ወይም ሌሎች ወገኖች መረጃ በመውሰድ በግብር

አወሳሰን የሥራ ሂደት በኩል በዴስክ ኦዲት በማጣራት አገልግሎቱ እንዲሰጥ ለደንበኞች አገልግሎት የሚተላለፍ ይሆናል።

17. <u>በውጪ ኦዲት ተመርምረው ስለሚቀርቡ የኦዲት ሪፖርቶች</u>

በልዩ ሁኔታ ተመዝግበው በባለሥልጣኑ ዕውቅና በተሰጣቸው የውጪ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርገው የሚቀርቡ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ ብቻ በመመስረት የአገልግሎት ጥያቄዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በደንበኞች አገልግሎት በኩል እንዲስተናገዱ ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ሪፖርት ማቅረብ እና ማስመርመር ግዴታ ስለመሆን</u>

18. <u>የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኃላፊነት</u>

በአገልግሎት ጥያቄ መነሻነት ኦዲት ከተደረጉ ግብር ከፋዮች ጋር በተያያዘ የኦዲት ሪፖርት በየወሩ ወሩ በገባ በ3 ቀን ውስጥ ለዋናው መ/ቤት የታክስ ኦዲት ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በባለሥልጣን በተዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ መሠረት ማቅረብ አለባቸው።

19. <u>ሪፖርት ስለማቅረብ</u>

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአገልግሎት ጥያቄ መነሻነት፦

1) ኦዲት ከተደረጉ ግብር ከፋዮች ጋር በተያያዘ የኦዲት ሪፖርት ወር በገባ በ3 (ሦስት) ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ ባዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ለዋናው መ/ቤት የታክስ ኦዲት ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ማቅረብ አለባቸው።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በግብር አወሳሰን የዴስክ ኦዲት እና በተመሳሽ ቡድን በኩል አገልግሎት የተሰጣቸውን ግብር ከፋዮች ወር በገባ በ3 (ሦስት) ቀናት ውስጥ ባለሥልጣኑ ባዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሰራር ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም በደንበኞች አገልግልግሎት በኩል በቀጥታ አገልግሎት የተሰጣቸውን ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ማቅረብ አለባቸው።

20. <u>ስለ ማስመርመር</u>

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሰጡትን አገልግሎት በዋናው መ/ቤት በሚመለከተው ዳይሬክቶሬት፣ እንደ አስፈላጊነቱ በዋናው ኦዲተር የማስመርመርና ተገቢውን ማብራሪያ የመስጠት ኃላፊት አለባቸው።

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>ልዩ ልዩ</u>

21. <u>የተሻሩ መመሪያዎች</u>

1) የግብርና ታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎች አነሳስ፣ የክፍያ ጊዜ ስምምነት እና የግብር ግዴታን ስለመወጣት በማረጋገጫነት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት (ክሊራንስ) አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 55/2003 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (2) (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) እና
2) ሌሎች ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች እና የአሰራር ማንዋሎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

22. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ -----------2009 ዓ.ም

ሞገስ ባልቻ
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር

Ethiopian Revenues & Customs Authority
Records & Documentation No 2

ቶቸመ ወልዴ
ሕግ ረቂቅና ስልጠና ቡድን አስተባባሪ